PEC ፓዝዌይ Pathway Education Consulting

ECD ETHIOPIAN CENTER FOR DEVELOPMENT

Pestalozzi Children's Foundation

የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም

ታኅሣሥ 2015

Trainee Self Introduction



Tell a brief personal background of yourself the occasion that you expect from this Training to the person near to you & let him introduce you to the participants

5 Minute

ይዘት

- መግቢያ
- ክፍል አንድ፡- ማስተማሪያ ቁሳቁሶች ምንነት እና ጠቀሜታ
- ክፍል ሁለት፡- የማስተማሪያ ቁሳቁስ ዓይነቶች
- ክፍል ሦስት፡- የመማሪያ ቁሳቁሶችን አዘገጃጀትና አጠቃቀም

ክፍል አንድ

የማስተማሪያ ቁሳቁሶች/ ሚዲያ ምንነት እና ጠቀሜታ

የስልጠናው ዓላማ

የክፍል ውስጥ መማር እና ማስተማርን በጣም አስደሳች እና ውጤታማ ለማድረግ የሚያገለግሉ የተለያዩ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን አዘገጃጀትና አጠቃቀም ማስተዋወቅ ነው

መግቢያ



Reflection and Discussion on the topic

ካለዎት ልምድ “የትምህርት ቁሳቁስ/ሚዲያን” እንዴት ይገጹታል?

በቡደን በቡድን በመደራጀት በ”ማስተማሪያ ቁሳቁስ” እና “በማስተማሪያ ሚዲያ” መካከል ስላለው ተመሳሳይነትና ልዩነት ተወያዩ።

የቀጠለ..

- የማስተማሪያ ቁሳቁስ” ወይም “የማስተማሪያ ሚዲያ” መምህሩና ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸውን ሁሉንም የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የሚያካትቱ ናቸው በማለት ሲተረጉሙት ሌሎች ደግሞ የኅትመት ሚዲያዎችን ብቻ በመወከል አገልግሎት ላይ የሚወሉ ናቸው ይሉታል።

- የማስተማሪያ ቁሳቁስ ማለት በአጠቃላይ የመማር ግብ እንዲሳካ መምህሩ የሚጠቀማቸው ሁሉንም ቁሳቁሶች የሚያካትት እንደሆነ ያስቀምጣሉ

የቀጠለ..

- የማስተማሪያ ቁሳቁስ” ወይም “የማስተማሪያ ሚዲያ” ስንል

- ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን
- ፎቶግራፎችን
- በመምህራን የተሠሩ ሥዕላዊ መግለጫዎችን
- ስንጠረዥችን፣ እውነተኛ ዕቃዎችንና ሌሎችም

- በአጠቃላይ ማስታወሻዎችን ጨምሮ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሁሉንም መሳሪያዎች ያካትታል።





The Iceberg Illusion
Success is an iceberg
WHAT PEOPLE SEE
SUCCESS!
WHAT PEOPLE DON'T SEE
Persistence
Dedication
GOAL
Failure
FAIL
Hard work
Sacrifice
THINGS I HAVE TO GIVE UP
1.
2.
3.
Good habits
Disappointment
@sylviaduckworth

የማስተማሪያ ቁሳቁስ ዓላማ



Reflection and Discussion on the topic

መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የማስተማሪያ

መሳሪያዎች ምን ምን ጠቀሜታ ይኖራቸዋል

ብለው ይገምታሉ?

The 4 Types of Team Members You Can Hire.mp4

የቀጠለ...

- በአጠቃላይ የመማሪያ ቁሳቁስ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተማሪውን የትምህርት አቀባበል ለማሳለጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ ለማድረግ ነው።

- በተጨማሪም የማስተማሪያ መሳሪያዎች አንድ የትምህርት ይዘት ከተሰጠ በኋላ ተማሪዎች ተፈላጊውን የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ ያግዛሉ።

@successpictures
@successpictures
ሚዲያ

The power of **Team Work**

Mis use of Materials

የማስተማሪያ ቁሳቁስን የምንጠቀምባቸው ምክንያቶች

1. ተማሪዎችን ማንነቃቃት

- በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን ትኩረት መሳብ ቁልፍ ተግባር ነው ።
- የማስተማሪያ መሳሪያዎች ድርሻ አላቸው ደግሞ የተማሪውን ትኩረት በመሳብ ረገድ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ።
- ተማሪዎች የማስተማሪያ መሳሪያዎችን በመመልከት አንዴ ከተነቃቁ አዳዲስ ንገሮችን ለመማር ንቁ ይሆናሉ።
- የማስተማሪያ መሳሪያዎች የተማሪውን የተለያዩ የስሜት ህዋሳት የመቀስቀስ ባህሪ አላቸው።Labratory work.mp4

2. መረጃን ለረጅም ጊዜ ለማቆየት ወይም ለማስታወስ መቻል

- ተማሪዎች ከመማሪያ ቁሳቁሶች ጋር ያላቸው ግንኙነት ባደገና የስሜት ህዋሳቶቻቸው ተሳትፎ በጨመረ ቁጥር ከትምህርቱ ያገኙት መረጃ በአእምሯቸው ውስጥ ለረጅም ጊዜ የመቆየት እድሉ ከፍተኛ ነው።

- በዚህ ምክንያት ትምህርቱ ውጤታማና ለብዙ ጊዜ ከተማሪው ጋር አብሮ የሚኖር ይሆናል።

Practical Work including field.mp4

3. ሁሉን አቀፍ መማርን ማመቻቸት

- በእውቀት(ኮግኒቲቭ)፣በስሜታዊ (አፌክቲቭ) እና በሳይኮሞቶር ተማሪዎች እድገት እንዲያሳዩ ይፈለጋል።
- ስለሆነም የተለያዩ ዓላማዎችን ለማሳካት የተለያዩ የመማሪያ ልምዶችን መጠቀም ያስፈልጋል፤ ይህም የተለያዩ የመማሪያ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ሊከናወን ይችላል።

4. የክፍል ውስጥ መማር ማስተማርን ለማደራጀት ማገዝ

- አንድን ይዘት ትክክለኛ በሆነና በቅደም ተከተል በተደራጀ መንገድ አንድን ይዘትን ለተማሪው ለማቅረብ ምስላዊ ወይም የቃል ማስተማሪያ ቁሳቁሶችን መጠቀም ያስፈልጋል
- ይህም በመምህሩና በተማሪዎች መካከል በክፍል ውስጥ በቃል እና በምስል መግባባት እንዲኖር ይረዳል
- ስለሆነም በቃል ወይም በምስል ተግባቦት ላይ ያሉ ጉድለቶችን ለማሸነፍ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን መጠቀም ያስፈልጋል Before and after Numbers.mp4

5.የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ ማገዝ

- የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ተማሪዎች በአጠቃላይ ስለትምህርት፣ በተለይ ደግሞ ስለ አንድ የትምህርት ዓይነት ወይም ይዘት ያላቸውን አመለካከት ለመለወጥ ይረዳሉ።

- ሥዕሎች፣ ሞዴሎች እና ሌሎች የማስተማሪያ ቁሳቁሶች የተማሪዎችን ቀና አመለካከት ለመቅረጽ ይረዳሉ።

6. ትምህርትን ተጨባጭ ወይም ተግባራዊ ማድረግ

- የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ንድፈ ሀሳባዊ ዕውቀቶች እንዴት ወደ ተጨባጭ ተግባራት እንደሚለወጡ ያሳያሉ።

- በክፍል ውስጥ የተጠናው የንድፈ ሀሳብ ዕውቀት በማስተማሪያ ቁሳቁሶች አማካይነት በተጨባጭ መልክ የሚታይ በመሆኑ ትምህርቱንም ውጤታማ ይሆናል። Laboratory Life of students.mp4

7. መማርን አስደሳች ማድረግ

- የማስተማሪያ ቁሳቁሶች በክፍል ውስጥ መማርን አስደሳች ለማድረግ ይረዳሉ።

- ተማሪዎች አዳዲስ የሆኑ የትምህርት ቁሳቁሶችን በመጠቀማቸውና በእነርሱም አማካይነት አዳዲስ ጽንሰ ሃሳቦችን በማግኘታቸው ይደሰታሉ። Motivating Students.mp4

8. የጽንሰ ሃሳብ ምስረታ

- የማስተማሪያ ቁሳቁስ በተማሪዎች ወይም በህጻናት አእምሮ ውስጥ ጽንሰሃሳብን የመመስረት ጉልበት አላቸው።
- የማስተማሪያ ቁሳቁስ ረቂቅ ጽንሰ ሃሳቦችን ተጨባጭ ያደርጋሉ።
- በዚህ ምክንያት ተማሪዎች የሚማሩትን በወጉ ስለሚረዱ ትምህርትን ብሽምደዳ ዘዴ ወደመማር አይሄዱም።



Group Work

በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አጭር ዕለታዊ እቅድ አዘጋጁ

1. **የቃላት ምስረታ**
2. **ማብዛት**
3. **ምስሪቶች**
4. **የመሬት ክፍሎች**

tea
TIME

ክፍል ሁለት

የማስተማሪያ ቁሳቁስ አዘገጃጀት ዓይነቶች

የማስተማሪያ ቁሳቁስ ዓይነቶች

የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን በተለያዩ መንገዶች የተለያየ ምድብ ይመደባሉ ከእነዚህም ውስጥ፡

- የማስተማሪያ ቁሳቁሶቹን ለተማሪዎቹ በሚሰጧቸው የልምድ ዓይነቶች መሰረት የሚመድበውና በኤድጋር ዴልን የተሞክሮ ኮን (Edgar Dale's cone of experience) ላይ ተመስርቶ የሚደረገው የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ምደባ አንደኛው ሲሆን

- ሌላኛው የማስተማሪያ ቁሳቁስ መመደቢያ መንገድ የማስተማሪያ ቁሳቁሶቹ በሚያነቃቁት ወይም በሚቀሰቅሱት ወይም በሚያነቃቁት የስሜት ህዋሳት ዓይነት ላይ ተመስርቶ የሚደረግ የማስተማሪያ ቁሳቁስ ምደባ ነው።

1. በተማሪው በተገኘው የተሞክሮ ዓይነት ላይ በመመርኮዝ የሚደረግ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ምደባ

- ይህ ምደባ በዴል (1969) የተሞክሮ ኮን ላይ የተመሰረተ ነው።
- የተሞክሮ ኮኑ ከታች ሰፋ ያለ መሰረት ሲኖረው ከላይ ደግሞ ሾጠጥ ያለ ጫፍ ያለው ነው።
- ከኮኑ መሰረት ወደ ኮኑ ጫፍ ባመራን ቁጥር ይበልጥ ተጨባጭ ከሆኑ ተሞክሮዎች ይበልጥ ረቂቅ ወደሆኑ ተሞክሮዎች የሚያመሩ የተለያዩ የተሞክሮ ደረጃዎችን እናገኛለን
- የምስሉ መሰረት በአብዛኛው እንደ እውነተኛ ቁሶች፣ ናሙናዎች፣ የመስክ ጉብኝቶች፣ ምልከታዎችና ሙከራዎች ባሉ የመማሪያ ቁሳቁስ አማካይነት የሚገኙ ቀጥተኛ ተሞክሮዎችን የሚወክል ነው።
- ከመሰረቱ ጀምረን ወደ ፊደላዊ ትእምርቶች በሄድን ቁጥር ደግሞ ደረጃ በደረጃ ረቂቅና ቀጥተኛ ባልሆኑ መንገዶች ወደምናገኛቸው ተሞክሮዎች እንሄዳለን ማለት ነው።
- እነዚህ ተሞክሮዎች በረቂቅነት ደረጃቸው ይለያያሉ ማለት ነው።



ግራፍ 1. የኤድጋር ዴል የተሞክሮ ኮን

የቀጠለ

- ከቀጥተኛና ተግባራዊ ተሞክሮ በሾጣጣ ቅርጽ ወደተወከለው ወደ ጽሁፋዊ ወይም ፊደላዊ ትእምርቶች በሄድን ቁጥር በየደረጃው ረቂቅነቱ እየጨመረ ይሄዳል፡፡
- በየደረጃው የተማሪዎቹ ተሳትፎ እየቀነሰ ስለሚሄድ ንቁ ከመሆን ይልቅ ኢ-ንቁ ወይም ፍዝ ወደመሆን እየተሸጋገሩ ይሄዳሉ፡፡
- የኮኑ የታችኛው ክፍል ወይም መሰረቱ በበርካታ የስሜት ህዋሳት ተሳትፎ (በማየት ፣ በመንካት ፣ በመሞከር ፣ በመስማት እና በማሽተት) የተገኘውን ተጨባጭ ተሞክሮ የሚወክል ሲሆን ፣ የኮኑ አናት ፣ የፊደላት ተምርቶች (ቃላት) በጣም ውስን የሆኑ የስሜት አካላትን የሚያሳትፉ እጅግ ረቂቅ የሆኑ መልዕክቶችን የሚወክል ነው፡፡
- ዴል (1969) እንደሚገልጸው በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የምናቀርበው ትምህርት በርካታ የስሜት ህዋሳትን ባሳተፈ ቁጥር ትምህርቱ ይበልጥ ተጨባጭና ውጤታማ ይሆናል፡፡

የቀጠለ

- ነገር ግን የረቂቅነቱ መጠን እየጨመረ በሄደ ቁጥር የተማሪዎች የመረዳትና የማስታወስ ሁኔታ እየቀነሰ ይሄዳል።
- ዴል እንደሚለው በመማር ማስተማር ሂደት ወስጥ በአጠቃላይ ሰዎች በድርጊት ከሚሳተፉበት ነገር 90%ን፣ ከሚጽፉት ነገር 70%ን፣ ከሚያዩትና ከሚሰሙት ነገር 50%ን፣ ከሚሰሙት ነገር 20%ን፣ ከሚያነቡት ነገር ደግሞ 10%ን ያስታውሳሉ።
- ስለዚህ ተሞክሮዎች ይበልጥ ተጨባጭ በሆኑ ቁጥር ይበልጥ የሰዎችን የመረዳት መተን ይጨምራሉ ማለት ነው።
- ይህ ማለት ግን ተጨባጭ ወይም ቀጥተኛ ተሞክሮ ለተማሪዎች እውቀትን ለማስተላለፍ መምህራን ሊጠቀሙበት የሚገባ ብቸኛው ውጤታማ ተሞክሮ ነው ማለት አይደለም።



ግራፍ 2. ንቁ (ቀጥተኛ)፣ ምስላዊ እና ትእምርታዊ ተሞክሮዎች



Group Work

1. የሚከተሉት የኮንፊሽየስ አባባሎች መልእክት ምን እንደሆነ አብራሩ።

“ያየሁትን እረሳለሁ።”

“የሰማሁትን አስታውሳለሁ።”

“የሰራሁትን እረዳለሁ።”

A. ቀጥተኛ (ገባሪ) ተሞክሮ

- ቀጥተኛ ቀይም ገባሪ ተሞክሮ የምንለው በበርካታ የስሜት ህዋሳት ተሳትፎ የሚገኝ አንድ እውቀት ወይም ተሞክሮ ነው።

- አንድን እውቀት ወይም ተሞክሮ ለማግኘት ከተጨባጭ ነገሮች ወይም ከቁሳቁስ ጋር ቀትተኛ ንክኪ ወይም መስተጋብር ማድረግን የሚጠይቅ በመሆኑ “በማድረግ መማር” ተብሎም ይጠራል።
-
- እንደ ዳል (1969) ገለፃ ፣ ከስር የመጀመሪያዎቹ የሶስት ደረጃዎች ማለትም ቀጥተኛ ፣ የተቀነባበረ ተሞክሮ ፣ እና ትውን (ድራማዊ) ቀጥተኛ (ገባሪ) ተሞክሮ በሚባለው ቡድን ውስጥ ይመደባሉ።

የቀጠለ

ሀ. ቀጥተኛ ተሞክሮ:

- ይህ ደረጃ ተማሪዎች በራሳቸው ነገሮችን በማከናወን የሚማሩበት ደረጃ ነው፡፡
- ተሞክሮው ቀጥተኛ ነው የሚባልበት ምክንያት ተማሪዎቹ የሚማሩት ከሚታዩ፣ ከሚዳሰሱ፣ ከሚሰሙ፣ ከሚቀመሱ፣ ከሚሸተቱ ነገሮች ወይም ቁሳቁሶች ጋር ቀጥተኛ መስተጋብር በማድረግ ተፈላጊውን መረጃ የሚሰበስቡበት ስለሆነ ነው፡፡
- ለምሳሌ የእንጨት ሥራ መስራት፣ ቋጠሮ መቋጠር፣ ቢስክሌት መንዳት፣ መኪና መንዳት እና መዋኘት የመሳሰሉት
- ይህ ዓይነቱ ተሞክሮ ለህይወት ከመማር ጋር ተዛምዶ ያለው ነው (ዳን 2015: 107, ማሂሸዋሪ 2016: 2)፡፡

ለ. የተቀነባበረ ተሞክሮ

- ይህ ደረጃ ተማሪዎች የቦታ እና የጊዜ ውስንነቶችን ለማሸነፍ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ትክክለኛ እቃዎችን፣ ሞዴሎችን፣ ቅርጾችን እና ናሙናዎችን በመጠቀም ልምድን ወይም መረጃን የሚያገኙበት ነው፡፡
- ሞዴሎች እና ቅርጾች በመጠናቸው ከፍ ቀይም ዝቅ ከማለታቸው በስተቀር የትክክለኛው ነገር ወይም ቁስ ግልባጭ ወይም አምሳያ በመሆናቸው የሚያስፈልገውን ተሞክሮ ወይም መረጃ ለተማሪው ለማስተላለፍ ብቃት አላቸው፡፡
- እንደቀጥተኛ ተሞክሮ የተሟላ ተጨባጭነት ባይኖረውም ጽንሰ ሃሳቦችን በተሻለና ተጨባጭ በሆነ ሁኔታ ለመረዳት ከተቀሩት የተሻለ ነው፡፡

የቀጠለ

ሐ. ትውን (ድራማዊ) ተሞክሮ

- ትወና (ድራማትዜሽን) ተማሪዎቹ ስለ ክስተቱ ወይም ስለ አንድ ፅንሰ-ሀሳብ የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በሚያስችል እንደገና በተገነባ ተሞክሮ ውስጥ የሚሳተፉበት እንቅስቃሴ ነው፡፡
- ድራማዊ ተሳትፎ ተማሪዎቹ በቀጥታ ሊያገኟቸው ከማይችሏቸው አንዳንድ እውነታዎች ጋር በተቻለ መጠን እንዲቀራረቡ ሊረዳቸው ይችላል።
- በዳንግ (2015: 105) መሠረት ተማሪዎች በድራማ ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ በአምስት አጠቃላይ ዘርፎች የተማሪዎችን ትምህርትና እድገት ያዳብራል።
- እነዚህም አካላዊ እድገት (ስነውበታዊ ክሂል)፣ ስነጥበባዊ እድገት (የድራማና የቲያትር ችሎታ)፣ የአእምሮ እድገት (የአስተሳሰብ ችሎታ)፣ የግል እድገት (ግለሰባዊ ችሎታ) እንዲሁም ማህበራዊ እድገት (በይነሰባዊ ችሎታ) ናቸው።

B. ምስላዊ (አይኮኒክ) ተሞክሮ

- ምስላዊ (አይኮኒክ) ተሞክሮ ምስሎችንና ሥዕሎችን መተርጎምን ያካትታል።
- በዚህ የተሞክሮ ደረጃ ውስጥ ያለ ተማሪ ብዙውን ጊዜ ተመልካች ሲሆን አንድን የትምህርት ይዘት ለመማር ምስሎችን ፣ ስዕሎችን ወይም ፊልሞችን ይመለከታል።
- ይህን ተሞክሮ ከቀጥተኛ ተሞክሮ የሚለየው ተማሪዎቹ በይዘቱ ላይ በቀጥታ ተሳታፊ የሚሆኑበት ሳይሆን የሚሆነውን ነገር የሚታዘቡበት ሂደት መሆኑ ነው።
- ከትክክለኛው ነገር ወይም ቁስ ጋር የተራራቀ በመሆኑ የሚያሳትፉቸው የስሜት ህዋሳት ከሁለት ወይም ከሶስት አይበልጡም።

የቀጠለ

ሀ. ርኡይ (የሚታይ) ተሞክሮ (ዴሞንስትሬሽን)

- ማሳየት (ዴሞንንስትሬሽን) ተማሪዎች አንዳንድ ነገሮች እንዴት እንደተከናወኑ የሚመለከቱበት መንገድ ነው። ስለአንድ ነገር መንስኤ ወይም ምክንያት ማስረጃዎችን የምናረጋግጥበት ወይም አቅርበን የምንናሳይበት ነው።
- ለምሳሌ የአንድን ማሽን አሠራር ወይም አጠቃቀም ማሳየንት ወይም የአንድን ምርት አመራረት ሂደት ማሳየትንም ይጨምራል።

ለ. የመስክ ጉብኝት (ጥናት)

- የመስክ ጉብኝት ተማሪዎች እንደ ሙዚየም ፣ ፋብሪካ ፣ ጂኦሎጂካል አካባቢ ወይም የተወሰኑ እጽዋት እና እንስሳት ያሉባቸውን ቦታዎችን በመጎብኘት ቅጥተኛ ዕውቀት የሚያገኙበት ትምህርትዊ ወይም ጥናታዊ ጉዞ ነው።

- የመስክ ጉብኝት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ወይም በቤተ ሙከራ ውስጥ ሳይሆን በእውነተኛ ወይም በተፈጥሯዊ አካባቢ በአካል በመገኘት የሆነ ነገርን እንዲያጠኑ እድል ይሰጣቸዋል።
- የመስክ ጉብኝት አተገባበር የራሱ መመሪያዎች ያሉት በመሆኑ ያንን መከተል አለበት

ሐ. ኤግዚቢሽኖች

- ኤግዚቢሽኖች የቁሳቁሶች ስብስቦች ናቸው። ቁሳቁሶቹ ተከታታይ ፎቶግራፎችን ፣ ሞዴሎችን ፣ ሰንጠረዦችን ፣ የሙከራ ማሳያዎችን ወይም የሳይንስ መሣሪያዎችን ፣ የስላይድ ፕሮጀክተርን ፣ ተንቀሳቃሽ ምስልን ፣ ኮምፒተርን እና ቴሌቪዥንን ያካትታሉ።

- በኤግዚቢሽን ውስጥ ተማሪው ቁሳቁሶችን መነካካቱ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ልክ እንደ ተመልካች ሆኖ መመልከት ይችላል።

- ተማሪው ቁሳቁሶችን ለመነካካት እድል ማግኘቱ የበለጠ የስሜት ሕዋሳትን የመጠቀም እድሉን ያሰፋለታል።

መ. ተንቀሳቃሽ ምስሎችና ትምህርታዊ ቴሌቪዥን

- ተንቀሳቃሽ ምስሎችና ትምህርታዊ ቴሌቪዥኖች ከመስክ ጉብኝት ይልቅ ጊዜንና ቦታን ይቆጥባሉ።
- በዳንግ (2015: 104) መሠረት ፣ ተንቀሳቃሽ ምስል እና ቴሌቪዥን አላስፈላጊ እና ተደጋጋሚ ይዘቶችን በማስወገድ በተመረጡ ነጥቦች ላይ ብቻ ሊያተኩሩ ይችላሉ።

ሮ. ትእምርታዊ (ሲምቦሊክ) ተሞክሮ

- ትእምርታዊ (ሲምቦሊክ) ተሞክሮዎች የንባብ እና የመስማት ምልክቶችን የሚያካትቱ በጣም ረቂቅ ልምዶች ናቸው። እነሱም፡-

ሀ. እይታዊ ትእምርቶች (ምልክቶች)

- እይታዊ ትእምርቶች (ምልክቶች) የምንላቸው እንደ ካርቱኖች ፣ ንድፎች ፣ ስዕላዊ መግለጫዎች ፣ ካርታዎች ፣ ግራፎች ፣ ፖስተሮች እና ገበታዎች ያሉ ቁሳቁሶች ናቸው።
- እነዚህ የትምህርት ቁሳቁሶች አንድን ረቂቅ ወይም ተጨባጭ ነገር የሚወክሉ ሲሆኑ ውክልናቸው በሰዎች ስምምነት ላይ የተመሰረተ ነው።

ለ. ተነጋሪ (ቃላዊ) ትእምርቶች

- እነዚህ እጅግ ረቂቅ ወይም ቀጥተኛ ያልሆኑ የእውነታ ውክልናዎች ናቸው።
- ተነጋሪ ትእምርቶች ሀሳቦች ፣ ፅንሰ-ሀሳቦች፣ ሳይንሳዊ መርሆች ፣ ቀመሮች ወይም በሌላ የቃል ትእምርትነት ውስጥ የሚገኝ የልምድ ውክልና ሊሆኑ ይችላሉ።
- እነዚህን ምልክቶች ከሚወክሉት ነገር ጋር የሚያመሳስላቸው ነገር የለም።
- በዘፈቀደ የተመረጡና ለክስተቶች ወይም ለልምዶች መጥሪያ ወይም ማስታወሻ ሆነው የሚያገለግሉ ምልክቶች ናቸው።

2. በሚያነቃቁት ስሜት መሠረት የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ምደባ

- ሌላው የማስተማሪያ ቁሳቁስን በሚያነቃቁዋቸው የስሜት ህዋሳት እና በሚያስተላልፉት መልእክት መሠረት የመማሪያ ሚዲያዎች የመመደብ መንገድ ነው።

- በዚህ የአከፋፈል ስልት መሠረት የማስተማሪያ ቁሳቁሶች (ሚዲያ) በአጠቃላይ በሦስት ቡድኖች ሊመደቡ ይችላሉ፤ ኦዲዮ ፣ ቪዥዋል እና ኦዲዮ-ቪዥዋል ተብለው። እናብራራለን።



ግራፍ 3. በሚያነቃቁት ስሜት መሠረት የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ምደባ

የቀጠለ

- **ሀ. የኦዲዮ ቁሳቁሶች**

- ይህ ምድብ እንደ ሬዲዮ እና ቴፕ ያሉ አናሎግ ቁሳቁሶችን፣ እንደ ሲዲ ፣ ዋቭ እና ኤምፒ3 ያሉ የድምፅ ፋይሎችን እና የመሳሰሉ ዲጂታል ቁሶችን ያካትታል።

- እነዚህ በቃል የሚተላለፉ መረጃውችን ያካተቱና መመሪያዎችን ለማቅረብ እንዲሁም የአእምሯዊ እና የሞተር ክህሎቶችን ትምህርት ለመስጠት ሊያገለግሉ ይችላሉ።

- አነስተኛ እምቅ ካሴት መቅረጫዎች ከተገኙ እንዲህ ዓይነት የድምፅ ሚዲያዎች በሠልጣኝ መምህራን አማካይነት ሊዘጋጁ ይችላሉ። ተማሪዎችም ሊሳተፉ ይችላሉ

- በተቀረጹ ድምጾች አማካይነት የሂሳብ መልመጃዎችን፣ የእንግሊዝኛ ሰዋሰውን እና እንግሊዝኛ የመናገር ክሂልን ማስተማር ይቻላል። ።

ለ. ቪዥዋል (የእይታ) ቁሳቁስ

- እነዚህ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች የማየት ስሜትን የሚቀሰቅሱ ናቸው። እነዚህንም ቃላዊ (የሕትመት) እና ሥዕላዊ ብሎ በሁለት ቦድኖች መክፈል ይቻላል። የህትመት ቁሳቁሶች ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸውን በከፍተኛ ቁጥር ሊታተሙ ወይም ሊባዙ የሚችሉ ሁሉንም የጽሑፍ ቁሳቁሶች ያጠቃልላሉ።

- እነዚህ ቁሳቁሶች እንደ መማሪያ መጻሕፍት፣ የማጣቀሻ መጽሐፍት፣ ኢንሳይክሎፔዲያ፣ መጽሔት፣ ጋዜጣ፣ የእጅ ጽሑፎች ወዘተ. ያሉ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ያካትታሉ።

ሐ. ኦዲዮ ቪዥዋል

- እንዚህ በቃልና በምስል ያሉ ስሜትን የሚቀሰቅሱ ሚዲያዎች ናቸው

tea
TiME

ክፍል ሦስት

የማስተማሪያ ቁሳቁስ አዘገጃጀት

የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት

- የማስተማሪያ ቁሳቁሶች የመማር ማስተማር ሂደቱን የሚያነቃቁ በጣም አስፈላጊ መሣሪያዎች ናቸው።
- ተማሪዎችን ከእውነተኛው ዓለም ጋር በማገናኘት ተሳትፏቸውን እንዲያሻሽሉ ያደርጋሉ እንዲሁም የትምህርት ይዘቶችን ታዋሽነትና የትማሪዎችን የመረዳት አቅም ይጨምራሉ።
- ለመማር ማስተማር ተግባር የሚውሉ የትምህርት ቁሳቁሶች ውስብስብናየተራቀቀ ቴክኖሎጂ ውጤቶች ወይም ቀለል ያሉ መሳሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ።
- ውስብስብ እና የተራቀቁ ቁሳቁሶች ተደራሽ በማይሆኑበት ጊዜ የተሻለው አማራጭ በአካባቢው ከሚገኙ ነገሮች በቀላል ወጪ ሊዘጋጁ በሚችሉና የተማሪውን ስሜት ሊይዙ በሚችሉ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች መጠቀም ነው።
- ትምህርት ቤቶች በዝቅተኛ ዋጋ ወይም ያለ ዋጋ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት ይችላሉ።

Reflection and Discussion on the topic

- በትምህርት ቤት ደረጃ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ልማት (የማምረት ሂደት) ውስጥ የሚከተሉትን አካላት ሚና ይፃፉ።
  - የትምህርት ቤት ርእሰ መምህር
  - መምህራን
  - ተማሪዎች
  - የአስተዳደር ሰራተኞች
  - የትምህርት ቤት ፀጥታ አካላት

Imagine what we can accomplish
when we work together
@successpictures
?
@successpictures

የዝግጅት ሂደት ደረጃዎች

- የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን የማልማት ሂደት ብዙውን ጊዜ ሶስት እርከኖች ያጠቃልላል
  1. የጥሬ ዕቃዎች መሰብሰብ
  2. መሳሪያዎቹን ማምረት እንዲሁም
  3. ጥበቃ እና ጥገና ናቸው።

- መምህራንና ተማሪዎች የዚህ ሂደት አካል ናቸው

ተማሪዎች መሳተፋቸው

- በተማሪዎቹ ውስጥ በራስ የመተማመን ስሜትን ይፈጥራል።

- ለማስተማሪያ ቁሳቁሶቹ ደህንነትም ጥበቃ እንዲያደርጉና ለክፍል ውስጥ አጠቃቀማቸው አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል።

- የተማሪዎችን የባለቤትነት ስሜት ከማሳደጉም በላይ ለትምህርት ቤቱ እና ለሀብቱ መጠበቅ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያዳብራል።

- ስዕላዊ ቁሳቁሶችን ማምረት ሂደት መምህራንና ተማሪዎች ከሚጠቀሙባቸው ቴክኒኮች ወይም ስልቶች መካከል

ሀ. ትሬሲንግ ዘዴ

- ትሬሲንግ አንድ ኦሪጂናል ከሆነ ምስል ገጽ ላይ ሳሳ ያሉ ወረቀቶችንና ፕላስቲኮችን በማስቀመጥ ከስር ባለው ሥዕል ውስጥ የሚታዩትን ዋና ዋና እና ዝርዝር ነገሮችን የመከተል እና ምልክቶችን የማድረግ ተግባር ነው፡፡

- ሁሉንም አስፈላጊ ክፍሎች መውሰድዎን እርግጠኛ በሚሆኑበት ጊዜ የራስዎን ዝርዝሮች መውሰድ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በጣም ብዙ በሆኑ ዝርዝሮች ነገሮችን በዚግ ስልት መውሰድ ያዳግታል፡፡

ለ. ሥዕሎችን የማሳደግ ዘዴ

- ሥዕላዊ የማስተማሪያ ቁሳቁስን በምንጠቀሙበት ጊዜ ከሚያጋጥሙ ነገሮች አንዱ መጠን ነው
- ይህንን ለማድረግ በብዙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሰፊው ጥቅም ላይ የሚውለው “የልኬት” ወይም “የስኩዌር” ዘዴ ነው (“ፍርግርግ” ዘዴ ተብሎም ይጠራል)።



ሐ. የማባዛት ዘዴ

- አንድ ጊዜ የአንድን ተጨባጭ ወይም ረቂቅ ቁስ ወኪል ከተመረተ ወይም ከተሰራ በኋላ ቀጣዩ ነገር የተሰራውን ነገር በርካታ ግልባጮች ሊሆን (የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ለክፍሉ ተማሪዎች ሁሉ እንዲደርሳቸው ካስፈለገ)

መ. ድጋፍ የማበጀት ዘዴ

- ይህ ዘዴ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ለረጅም ጊዜ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ከኋላቸው ድጋፍ እንዲኖራቸው የማድረግ ተግባር ነው።
- የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ረጅም አገልግሎት እንዲሰጡ አንድም ከጠንካራ ጥሬ እቃ መስራት አለዚያም ደጋፊ በሆኑ ሌሎች እቃዎች ማጠናከር (በማያያዝ ወይም በማጣበቅ) ያስፈልጋል።

የማስተማሪያ ቁሳቁሶች አጠቃቀም

- የማስተማሪያ ቁሳቁሶች በራሳቸው የመማር ማስተማሩን ሥራ ለማሻሻል ወይም ለማዳበር ብዙ የሚረዱ ሳይሆኑ የእነሱ ዋጋ ወይም እሴት በመምህራኑ ወይም ቁሳቁሱን በሚተቀመው ባለሙያ ችሎታ ላይ የተመሠረተ ነው(በሀይኒች እና ሌሎች (1996)፣ በአብርሃም (2001: 24)

- የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም መምህራን የሚከተሉትን መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳቦች ማጤን አለባቸው፡፡
  - ✓ የተማሪዎችን ባህሪ መተንተን
  - ✓ ዓላማዎችን በትክክል መግለጽ
  - ✓ የማስተማሪያ ቁሳቁሱን መምረጥ
  - ✓ የማስተማሪያ ቁሳቁሱን መጠቀም
  - ✓ ተማሪውን ማሳተፍ
  - ✓ መገምገምና መከለስ ናቸው፡፡



Group Work

- በቡድን በመሆን ከአካባቢ ቁሳቁሶች ብቻ በመጠቀም አንድ ሚዲያ አዘጋጁ (የተማሪዎችን ከሶስቱም ዶሜን አንጻር ሊለለሳትፍ የሚችል)

አመሰግናለሁ